Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

ጁን 2021

# የቨርቹወል አካደሚ ማመልከቻ

ሞንትጎመሪ ቨርቹወል አካደሚ

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

Rockville, Maryland 20850

***መምርያዎች፡-*** እባክዎ ወደ ቨርቹወል አካደሚ ለሚያመለክት ለእያንዳንዱ(ዷ) ተማሪ አንድ ቅጽ ይሙሉ። ተማሪዎች በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ብቁ የሚያደርጋቸውን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።

## የፕሮግራም አጠቃላይ ምልከታ

- ለ 2021-2022 የትምህርት ዓመት፥ ፕሮግራሙ ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ትምህርታቸው በአስቸጋሪ ሁኔታ የሚገኙ ተማሪዎችን ያገለግላል። በተናጠል የሚቀርቡት ሰነዶች በሙሉ፣ ለመግባት የሚያስችላቸውን ጥያቄዎች በሙሉ የሚመልሱ መሆን አለባቸው። እንደዚህ ዓይነት ማስረጃዎች ከሌሉ፣ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ስለሚያረጋግጥ ማስረጃ የ MCPS ሰራተኞችን በማነጋገር ማግኘት ይቻላል።
- ፕሮግራሙ በሳምንት አምስት ቀን ሙሉ በሙሉ በኢንተርኔት አማካኝነት ለማስተማር የሚያስችል አጠቃላይ ፕሮግራም ነው።
- ተማሪዎች ፕሮግራሙን በኮምፒዩተርና በኢንተርኔት አማካኝነት በቀጥታ በሳምንት አምስት (5) ቀናት ሙሉ በሙሉ የቨርቹወል አካዳሚውን ትምህርት የሚከታተሉ ሲሆን በ MCPS ተቀባይነት ያለው የአጠቃቀም ፖሊሲ IGT-RA መከተል ይኖርባቸዋል።
- እድሜአቸው ከ 12 ዓመት በታች የሆኑ ተማሪዎች በፕሮግራሙ ለመሣተፍ እንዲችሉ በትምህርት ሠዓት አዋቂ/ጎልማሳ ሰው ሊቆጣጠራቸው ይገባል።
- ቨርቹወል አካደሚ መግባት 2021-2022 የትምህርት ዓመቱን በሙሉ ለመከታተል ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ይሁን እንጂ ተማሪዎች ወደ ተመደቡበት ትምህርት ቤት ተመልሰው ለመግባት ለዝውውር በተመደቡ ጊዜያት ሊያመለክቱ ይችላሉ። የዝውውር ሁኔታ የሚወሰነው በቦታ እና በፕሮግራም መገኘት ላይ የተሞረኮዘ ነው።
    - ኤለመንተሪ/መካከለኛ ደረጃ (ከመዋእለ ህጻናት እስከ 8ኛ - K-8 ክፍሎች)፡- የዝውውር ጊዜ ሊሆን የሚችለው እያንዳንዱ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ በሚጠናቀቅበት ወቅት ይሆናል።
    - ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (ከ 9-12ኛ ክፍል)፡- የዝውውር ጊዜ ሊሆን የሚችለው በእያንዳንዱ ሰሚስተር መጨረሻ ላይ ነው።
- ተማሪዎች በየዓመቱ ወደ ፕሮግራሙ ለመግባት እንደገና ማመልከት ይጠበቅባቸዋል።
- ለተማሪዎች የቴክኖሎጂ ተደራሽነት የሚኖረው አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ነው።

## ለፕሮግራም ብቁ ስለመሆን

- ተማሪዎች ለቨርቹወል አካደሚ ማመልከት የሚችሉት፡-
    - ተማሪው(ዋ) ወይም የተማሪው(ዋ) ቤተሰብ ከጤና ጋር በተያያዙ ችግሮች ወይም በሌላ ምክንያት የደረሰ ጉዳት በቨርቹወል ትምህርት ተሞክሮ የሚሻሻል መሆኑ ከታወቀ ወይም በቨርቹወል ትምህርት ስኬታማነት ሁኔታው ሊለወጥ እንደሚቻል ታስቦ ከሆነ የሚያመለክቱበት ምክንያት፥ ትምህርት የተከታተለ(ች)በትን እና የተማረ(ች)በትን ሠነድ ከዚህ በታች በሚገኘው (ሌላ/Other) ስር ሠነዶች መቅረብ አለባቸው።
        - ቨርቹወል አካደሚ ለመግባት የሚፈልጉ ወላጆች/ሞግዚቶች/ብቁ የሆኑ ተማሪዎች በአካል ከመማር ይልቅ ቬርቹወል ትምህርት ያስፈለገበትን አስቸጋሪ ሁኔታ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው።
        - በጤንነት ምክንያት በጤና ባለሙያ የሚሰጥ ህክምና እየተከታተለ(ች) የሚገኝ-የምትገኝ ተማሪ ወይም የቅርብ ቤተሰብ የሆነ(ች) ሰው ለኮቪድ-19 የተጋለጠ(ች) እንደሆነ የበለጠ አስቸጋሪ ሁኔታ ሊሆንባቸው እንደሚችልና ቨርቹወል ትምህርት ላይ መሳተፍ ሁኔታውን ሊያሻሽል እንደሚችል ከጤና ባለሙያ የተሰጠ ማስረጃ መቅረብ አለበት። በተጨማሪም ማመልከቻውን የሚደግፉ ማንኛውንም ማስረጃዎች/ማቴሪያሎች እና የግምገማ ሒደቶችን የክፍል ደረጃ፥ የትምህርት ክትትል፥ ተሳትፎ እና ሌሎች ማስረጃዎችን ሊጨምር ይችላል። ማመልከቻው ከቀረበ በኋላ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የሚያሳይ እንደዚህ ዓይነት ሰነዶች ከሌሉ ከMCPS ሰራተኞች ጋር በመነጋገር ማግኘት ይቻላል።
    - ለሁለተኛ ደረጃ ብቻ - ክሬዲት ለማሻሻል፥ ለኢንተርንሽፕ ወይም የሥራ ልምድ ለማግኘት፥ CTE program ለማሟላት ወይም ወደ ሞንትጎመሪ ኮሌጅ ለመግባት፥ ወይም ሙሉ ጊዜ በሚወስዱት ኮርስ ላይ ተጨማሪ ትምህርት ለመውሰድ መርሃግብር/የጊዜ ሠሌዳን ማመቻቸት ያስፈልጋል።
- ተማሪዎች በሜሪላንድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች መሆን አለባቸው
- ተማሪዎች ብቁ ለመሆን በ MCPS ት/ቤት የሚማሩ መሆን አለባቸው። እቤት ውስጥ የሚማሩ ወይም የግል/የህዝብ ያልሆነ ት/ቤት የሚማሩ ለቨርቹወል አካደሚ የሚያመለክቱ ተማሪዎች ከማመልከታቸው በፊት በ MCPS ት/ቤት መግባት አለባቸው። (ትምህርት ቤትዎን ያግኙ/Find your School -https://gis.mcpsmd.org/SchoolAssignmentTool2/)

## የተማሪ መረጃ

**የተማሪ ስም፡-** ____________________ **የተማሪ መታወቂያ፡-**____________

**ተማሪው(ዋ) የተወለደ(ች)በት ቀን፡-** ______/_______/______ **በ 2021-2022 የትምህርት ዓመት የተማሪው(ዋ) የክፍል ደረጃ**_____

**ለ 2021-2022 የ MCPS ትምህርት ቤት፡-**___________________________________

## የምዝገባ አማራጮች፡-

**ከመዋእለ ህጻናት እስከ 8ኛ (K-3) ክፍሎች**
ከመዋእለ ህጻናት እስከ ስምንተኛ (K-8) ወደ ፕሮግራሙ የሚገቡ ተማሪዎች ቨርቹወል አካዳሚ የሚገቡት ለሙሉ ጊዜ ይሆናል።

**የሚያመለክቱበት ምክንያት፡-**
ወደ ቪርቹዋል አካዳሚ የምታመለክትበትን-የምታመለክችበትን ምክንያት ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው የበለጠ ይገልጸዋል? በሚመለከተው ሁሉ ላይ ምልክት ይደረግ።

- ሙሉ ጊዜ ለመግባት የማያበቃ ምክንያት
  - ☐ የተማሪ ጤና ስጋቶች (የአእምሮ ጤናን ጨምሮ)
  - ☐ የቤተሰብ ጤና ስጋቶች
  - ☐ ሌላ፥ ይግለጹ፡-______________

**ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (High School)**

- ☐ ሙሉ ጊዜ -ወይም- ☐ ከፊል ጊዜ

**የምታመለከት(ች)በት ምክንያት፡-**
ወደ ቪርቹዋል አካዳሚ የምታመለክትበትን-የምታመለክችበትን ምክንያት ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው የበለጠ ይገልጸዋል? በሚመለከተው ሁሉ ላይ ምልክት ይደረግ።

- ሙሉ ጊዜ ለመግባት የማያበቃ ምክንያት
  - ☐ የተማሪ ጤና ስጋቶች (የአእምሮ ጤናን ጨምሮ)
  - ☐ የቤተሰብ ጤና ስጋቶች
  - ☐ ሌላ፥ ይግለጹ፡-______________
- ከፊል ጊዜ ለመግባት ምክንያቱ ምንድነው
  - ☐ ለ Montgomery College/CTE የጊዜ ሠሌዳ ማሟላት ስላስፈለገ
  - ☐ የተፈቀደ መርሃግብር መጣበብ
  - ☐ ከትምህርት ቀን ውጪ ተጨማሪ ኮርሶች
  - ☐ ከትምህርት ቀን ውጪ ውጤት/ክፍል ለማሻሻል
  - ☐ ክሬዲት ለማሟላት
  - ☐ ሌላ፥ ይግለጹ፡-______________

## የፕሮግራም መግለጫዎች

ቨርቹወል አካዳሚ ውስጥ ስመዘገብ እኔ መገንዘብ ያለብኝ፡-

- የቨርቹወል አካደሚ ተደራሽነትና ፕሮግራም ሊሰጥ የሚችለው የባጀትና የሠራተኛ ምደባዎች ከተሟሉ ነው።
- የክፍል ሥራዎች በሆምስኩል በሚሰጡት ሥራዎች ላይ የተመሠረቱ አይደሉም። ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ከሚማሩት ተማሪዎች ጋር በትምህርት ገበታ ላይ ላይሆኑ ይችላሉ፥ እንዲሁም በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ፕሮግራምና በሠራተኞች ምደባ ላይ የተመረኮዘ ሊሆን ይችላል።
- በግል ሁኔታ ላይ የተመሠረተ የትምህርት ፕሮግራም-Individualized Education Program (IEP) ወይም 504 plan ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የማመልከቻ ሒደቱ የ IEP ወይም 504 ስብሰባን ይጨምራል። ይኼውም በቨርቹወል ትምህርት ቤቱ የትኞቹ ድጋፎች፣ አገልግሎቶችና ማረፊያዎች እንደሚኖሩ የመገምገም፣ የመወያየትና የመወሰን ዓላማ ያለው ነው። በሜሪላንድ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ውጪ ነዋሪ ለሆኑ ተማሪዎች ላይሰንስ ባለው አካል የሚሰጡ አኮሞዴሽኖች እና የስፔሻል ኢጁኬሽን አገልግሎቶች አይሰጡም።
- አንዳንድ የፕሮግራሙ ገጽታዎች በአካል መሳተፍ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን በዚህ ሳይወሰን ስለ ደህንነት እና ሪፖርት መጠይቆችን (Regulation ILA-RA, Assessments with Security and Reporting Requirements) የስቴት እና የአካባቢ መስፈርቶችን ከማሟላት ጋር የተያያዙ ምዘናዎችና ግምገማዎች አስፈላጊ ናቸው። በነዚህ ሁኔታዎች ተማሪዎች የራሳቸውን መጓጓዣ መጠቀም ይኖርባቸዋል።
- ፕሮግራሙ ለመመረቂያ ለማዘጋጀት የሚሰጣቸው ዋና ዋና ኮርሶች ውስን ናቸው።
- በአሁኑ ወቅት በ "MCPS specialized/signature program" የሚገኙ ተማሪዎች ከዚያ ፕሮግራም ወጥተው ወደ ቨርቹወል አካደሚ ሊገቡ ይችላሉ። ተማሪዎች ወደ "MCPS specialized/signature program" ተመልሰው መግባት የሚፈልጉ ከሆነ እንደገና ማመልከት ይጠበቅባቸዋል።
- የአንድ ዓመቱ ስምምነት ከመጠናቀቁ በፊት የሚቀርቡ የዝውውር ጥያቄዎች በተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት የሠራተኛ መገኘት፥ የቦታ መገኘት፥ እና በፕሮግራም መገኘት ላይ የተሞረኮዘ ሲሆን በማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ እና በሰሚስተር የዝውውር ወቅት ላይ ባሉ ክፍት ጊዜዎች ብቻ የሚታዩ ይሆናል።

## ፕሮግራሙን ስለመቀበል/ስምምነት

❏ ይህ(ች) ተማሪ ቨርቹወል አካዳሚ ላይ እንዲሳተፍ-እንድትሳተፍ ተስማምቻለሁ።

## ፊርማ

በዚህ ቅጽ ላይ የተካተቱት ሁሉም መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ እናም ይህን ስምምነት ለመስጠት ስልጣን እንዳለኝ አረጋግጣለሁ።

ወላጅ/ሞግዚት/ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ ስም (ይጻፉ)፡-________________ ቀን፡- ___/___/___

ወላጅ/ሞግዚት/ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ ፊርማ፡- __________________ ቀን፡- ___/___/___